Open For Ad

# ንግድና ልማት

ሰኔ / ሐምሌ 2016 እትም ☎ 011-5573544 ✉ 2458 E-mail: info@addischamber.com www.addischamber.com

## አዲስ ቻምበር የመካከለኛ ጊዜ የስትራቴጂክ እቅድ አፈጻጸም ግምገማን አካሄደ

**በስታፍ ሪፖርተር**

አዲስ ቻምበር የግሉን ዘርፍ ተወዳዳሪና ውጤታማ ለማድረግ በማሰብ የተለያዩ ግቦችና አላማዎች ያሉት የአምስት አመት የስትራቴጂክ እቅድን በማዘጋጀት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል:: አሁን ላይ ደግሞ ምክር ቤቱ የመካከለኛ ጊዜ የስታራቴጂክ እቅድ ግምገማን በማድረግ በእቅድ ተይዘው የተከናወኑ፤ ያልተከናወኑ ፤ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም የመፍትሄ እርምጃዎች ላይ ትኩረቱን ያደረገ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችን ያሳተፈ ተከታታይ ውይይቶችን አካሂዷል:: ይህን መነሻ በማድረግ ምክር ቤቱ የ2017 ኣ.ም እቅድ ውይይት የተደረገ ሲሆን በእቅድ የተካተቱ ዋና ዋና ተግባራትና የወደፊት አቅጣጫዎች እና የሚያጋጥሙ ታሳቢዎችና ስጋቶች ላይ ጥልቅ ውይይት አካሂዷል:: በቀጣይም በምክር ቤቱ የቦርድ አመራር ጸድቆ ተግባራዊ እንደሚደረግ ተገልጿል::

## አዲስ ቻምበር በግብርና ማቀነባበር ዘርፍ ለተሰማሩ አባላቱ በኩባንያ መልካም አስተዳደር ምንነት ላይ ያተኮረ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ሰጠ



**በይድነቃቸው አለማየሁ**

የአዲስ ቻምበር የዳሬክተሮች ኢንስቲትዩት ያዘጋጀው ይህ ስልጠና ቀደም ሲል ለባንክ አመራሮችና የዳሬክተሮች ቦርድ አባላት ሲሰጥ የነበረው ስልጠና ቀጥሎ ነው የተሰጠው:: ስልጠናውን የሰጡት ጥላየ ካሳየ ( ፒ.ኤች.ዲ) ንግድ እንዲቀጥልና ዘላቂ እንዲሆን በጥሩ መሰረት ላይ መጣል አለበት ብለዋል ::ከዚህ ውስጥ አንዱ መሰረት የኩባንያ መልካም አስተዳደር መሆኑን ጠቅሰዋል :: የኩባንያ መልካም አሰተዳደርን በተመለከተ ገለፃ ሲያደርጉ ፤ አንድ ድርጅት ፖሊሲዎች ፣ ህጎች ፣ ደንቦች ሊኖሩት ይገባል ያሉት ጥላየ ( ፒ.ኤች.ዲ) ይህም ድርጅቱ ውስጥ ያሉትን ሰራተኞች እንዲሁም ከውጭ ያሉ የተለያዩ አካላት ለማገናኘት የሚያስችል መሳሪያ መሆኑን ጠቁመዋል:: በመሆኑም ግንኙነቶችን የተሳለጠና ውጤታማ በማድረግ የኩባንያው አስተዳዳሪዎች

ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## አምራቾች ከምርት በፊት መልሶ መጠቀምን ከግምት ማስገባት እንዳለባቸው ተገለጸ

**በሰናይት እሸቱ**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለአነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ ለሚገኙ ድርጅቶች በፕላስቲክ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋልን የተመለከተ ስልጠና ሰጥቷል:: ስልጠናው የፕላስቲክ ውጤቶችን ከአንድ ግዜ በላይ መጠቀም እንዲቻል የንግዱ ማህበረሰብ ድርሻዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው::

ስልጠናውን የሰጡት የፔትኮ ኢትዮጵያ ሃላፊ ወ/ሮ ምህረት ተክለ ማርያም ሲሆኑ የንግዱ ማህበረሰብም የፕላስቲክ ውጤቶችን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል እረገድ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲያመጣ እና እንዲተገብር መበረታታት እና መደገፍ እንዳለበት አንስተዋል::

የፕላስቲክ ቆሻሻዎች ውሃን በመበከል :የእንስሳትን ተፈጥሮአዊ አኗኗር በማዛባት እንዲሁም ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሻገር ችግር የሚያስከትሉ ናቸው::

ስልጠናውን የሰጡት ባለሞያ



እንዳነሱት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሚመነጨው ቆሻሻ 5.2 በመቶ የሚሆነው የፕላስቲክ ቆሻሻ ሲሆን በብዛት የሚመነጨውም ከፍተኛ ገቢ ካለው የማህበረሰብ ክፍል መሆኑን አስረድተዋል፡ይህ ደግሞ የማህበረሰብ የፍትህ ጥያቄን ሊያስነሳ የሚችል መሆኑን ጠቁመዋል::

የፕላስቲክ ቆሻሻን በመሰብሰብ ለመልሶ ጥቅም እንዲውል በማድረግ ዘርፍ የተሰማሩ አንቀሳቃሾች የቦታ ከጤና ጋር የተያያዙ እና የደህንነት እንዲሁም በደላሎች መሃል መግባት የሚከሰቱ ችግሮች እንቅፋት እንደሚሆኑባቸው ተጠቅሷል::

አምራቾች ለሚያመርቷቸው ምርቶች ማሸግያ የሚጠቀሟቸው ፕላስቲክ ግብአቶችን ከአንዴ በላይ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ አድርገው በትኩረት አለማምረታቸው፡በቀጣይ ኢኮኖሚ ውስጥ እንዲቆዩ እና እንዲያገለግሉ ስለማያደርጋቸው በዘርፉ ለተሰማሩት እንቅፋት እንደሆነ ተጠቅሷል፡ ለዚህም የፕላስቲክ ማሸግያዎች ላይ የሚካተቱ ቀለሞች እንደማሳያ ቀርቧል::

ፕላስቲክን እንደግብአት ከሚጠቀሙት የምግብ እና የመጠጥ ኢንዱስትሪው ሰፊውን ድርሻ የሚይዝ ቢሆንም ከኢንዱስትሪው የሚወጣው የፕላስቲክ ውጤት አንድ ግዜ ብቻ ጥቅም ላይ ሚውል በመሆኑ ይህ አሰራር ሊቀየር እንደሚገባ አንስተዋል::

ዘርፉ በቂ ባይባልም የህግ ድጋፎች ያሉት ቢሆንም በተናጠል በፕላስቲክ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ ያተኮረ የህግ ማእቀፍ አለመኖሩም መሻሻል የሚገባው ነው ተብሏል::

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት አረንጓዴ ኢኮኖሚን ከማሳደግ አንጻር ከተለያዩ አጋር ድርጅቶች ጋር የሚሰራ ሲሆን የፕላስቲክ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር የተካሄደው ስልጠናም የዚሁ አካል መሆኑ ተጠቁሟል::

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ**

**50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**

**ዋና አዘጋጅ**
አሸናፊ ምትኩ

**ዲዛይነር**
zgirmamecha@gmail.com

**ዐምደኞች**
ይድነቃቸው አለማየሁ
አሸናፊ ምትኩ
ሰናይት እሸቱ
ከፍያለው ዋሲሁን
ካሳሁን ማሞ

**የኤዲቶሪያል አባላት**
ስዩም ጫኔ-ሰብሳቢ
ካሳሁን ማሞ - አባል
አሸናፊ ምትኩ - አባል
አቶ ደሳለኝ ደጀን - አባል
አቶ የሀንስ ወ/ገብርኤል - አባል

**በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እየተዘጋጀ የሚወጣ ጋዜጣ 50ኛ ዓመት እትም**

**ADDIS BUSINESS**
ሰኔ / ሐምሌ 2016 እትም



TEL. 011-5518055 | 011-5519713
011-5155221
Fax. 011-5511479 P.O.BoX. 2458


# ርዕሰ አንቀጽ

## የሚዲያ ሚና ለንግድና ምጣኔሀብታዊ እድገት እውን እንዲሆን የበኩላችንን እንወጣ!

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት አስተዋጾ ከሚያደርጉ ተቋማት መካከል የመገናኛ ብዙሀን ይገኙበታል። እነዚህ ተቋማት የአንድን ሀገር ንግድና ኢኮኖሚ መረጃዎችን በማዳረስ ፤ ኢንቨስትመነት እንዲስፋፋ ፤ የውጭ ባለ ሀብቶች በሀገር ውስጥ ገብተው ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚጫወቱት ሚናቸው ከፍተኛ ነው።

ከዚህም ባለፈ የሚዲያ ተቃማት በንግድና ኢንቨስትመንት መስክ ለተሰማራው ህብረተሰብ ወቅታዊ መረጃ በማቅረብ የግሉ ዘርፍና የመንግስት ፖሊሲ አውጪዎች የንግድና ኢንቨስትመንት ነክ ጉዳዮች ላይ መረጃ እንዲለዋወጡና የመፍትሄ ሀሳብ እንዲያፈልቁ በመድረክነት በማገልገል የግሉ ዘርፍ ማነቆዎች እንዲሻሻሉና የግሉ ዘርፍ ከብሄራዊ ኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ያለውን አስተዋፅኦ አጠናክሮ እንዲቀጥል ጉልህ ሚናን ይጫወታሉ። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ንግድ ምክር ቤቱ አጋርነትን እንደ አንድ ቁልፍ መሳሪያ በመጠቀም ከሚመለከታቸው የመገናኛ ብዙኃን አካላት ጋር ተቀራርቦ በመስራት ላይ ይገኛል።

ንግድ ምክር ቤቱ ጠንካራና ተወዳዳሪ የግል ዘርፍ እንዲፈጠር ተነሳሽነትን በመውሰድ አመታዊ የሚዲያ ቀንን በማክበር የሚዲያ ሀላፊዎች፤ ጋዜጠኞች እና የህዘብ ግንኙነት ባለሙያዎች በአንድ ላይ የሚገናኙበትና የልምድ ልውውጥ የሚያከናውኑበት እለትን ፈጥራል።

ይህ ቀን በተለይም ምክር ቤቱ በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ለሚያደርገው አስተዋጽኦ ሚዲያዎች ከጎ በመሆን ላደረጉት ትብብርና የሚዲያ ድጋፍ እውቅና የሚሰጥበት ቀን ነው። በዚህም ሙያዊ እና ማኅበረሰባዊ ሥነ ምግባርን በጠበቀ መንገድ መፍትሔ ጠቋሚ እና ለአዎንታዊ ተግባራት የሚያነሣሡ የንግድና ኢንቨስትመንት መረጃዎች የሚሰራጩበት መንገድን ከሚዲያዎች ልምድ የሚካፈልበት ሲሆን የመገናኛ ብዙኃን ጋዜጠኞች በእውቀት ላይ የተመሰረተ ስራ እንዲሰሩና ለሀገራችን የኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ምክር ቤቱ በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያቀርባል።

ከዚህም ባለፈ በሚዲያ ተቋማትና በንግድ ም/ቤታችን መካከል ያለው የትብብር መንፈስ እና አጋርነትም ከዚህ በላይ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ምክር ቤቱ በጽኑ ያምናል። በተለይ መረጃ የሃይል ምንጭ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ልማት ሀሳብ መቀመሪያ፣መጠንሰሻ እና ማስተጋቢያ መድረክ መሆኑን በመረዳት ንግድና ኢንቨስትመንት አለም አቀፋዊ ገጽታ ተላብሶ ንግድ ድርጅቶችም ሆኑ አገሮች በከፍተኛ የውድድር ትንቅንቅ ውስጥ በገቡበት በአሁኑ ወቅት የሀገራችን ነጋዴዎች ለሀገር ውስጥም ሆነ ለአለም አቀፍ ገበያ የሚያቀርቧቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች ተወዳዳሪነት እንዲያጎለብቱ የተጠናከረ የቢዝነስ ትንታኔዎች እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች በመገናኛ ብዙሃን ማስተላላፍ ዘመኑ የሚጠይቀው ጉዳይ በመሆኑ የሚዲያ ተቃማትና ባለሙያዎች ሀገራዊ ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ምክር ቤቱ ጥሪ ያቀርባል!

# አዲስ ቻምበር በግብርና ማቀነባበር ዘርፍ ለተሰማሩ አባላቱ...



**ከ ገጽ 1 የዞረ**

ወይንም እነሱን የሚወክሉ ሰዎች ያለውን ስርዓት ፣ ህግ እና ፖሊሲ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሊያውሉ ይገባል ብለዋል ::

አክለውም ኩባንያዎች የኩባንያ መልካም አስተዳደርን በድርጅቶቻቸው ውስጥ ቢተገብሩ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያጋኛሉ ያሉት ጥላየ ካሳሁን ( ፒ.ኤች.ዲ) ፤ የኩባንያ መልካም አስተዳደርን መተግበር በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ኩባንያ እንዲሆን ያስችለዋል :: ሌላው የንግድ ድርጅቶች በደንበኞቻቸው ፣ በምርት አቅራቢዎቻቸው እንዲሁም በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ተቀባይነት ሲያገኙ የማደግ እድላቸው ከፍተኛ እንዲሆን ማድረግ ሌላኛው እንደሆነ አንስተዋል:: በመሆኑም በኩባንያ መልካም አስታደደር መርህ ተከትሎ የሚመራ ኩባንያ እድገቱ እና ትርፋማነት ብሎም የመስፋፋት እድሉ ከፍተኛ የማድረግ እድል አለው ብለዋል ::ይሁንና የኩባንያ መልካም አስተደደርን ተግባራዊ የማያደርጉ የቢዝነስ ድርጅቶች ባለህበት እርገጥ በማድረግ በሂደት መወዳደር ሰለማይችል ከገቢያ ሊወጣና ብሎም ሊከስም የሚችልበት እድል የሰፋ መሆኑን ጠቅሰዋል ::

ይህም የሚመነጨው ድርጅቱን የሚመሩ አካላት አቅምና ችሎታ አለመኖር አንዱ ሲሆን ለኩባንያ

መልካም አስተዳደር ያላቸው እይታ ትክክል አለመሆኑን በዋናነት አንስተዋል:: ድርጅቱን በሚመሩ አካላት ፣ ባለድርሻ አካላት እና የቦርድ አባላት መካከል የሚፈጠር አለመስማማትና መጠላለፍ ለኩባንያ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚደረገውን ጥረት የሚያበላሽ መሆኑን አንስተዋል ::

በኢትዮጳያ የኩባንያ አስተዳደርን እንዳይተገበር ዋነኛ ችግር ሆነው ከሚቀመጡት መካከል የኩባንያ መልካም አሰተዳደር ሚናን አለመረዳት ፣ በቂ በጀት አለመመደብ እንዲሁም በባለ አክሲዮኖች እና ኩባንያውን በሚመሩ የስራ ኃላፊዎች መካከል መልካም ግንኙነት አለመኖር መሆናቸውንም ጥላየ ካሳሁን ( ፒ.ኤች. ዲ) ጠቅሰዋል::

ይህ ማለት በኢትዮጵያ የኩባንያ መልካም አሰተዳደር ደካማ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም ያሉት ጥላየ ( ፒ.ኤች. ዲ) ብሄራዊ ባንክ ከሚሰጠው ጠንካራ የቁጥጥርና ክትትል አሰራር የተነሳ የባንክ ዘርፉ ትርፋማ መሆኑን አንስተዋል ::ይህም ሊሆን የቻለበት ባንኮቹ ባላቸው ማኔጅመንት ብቻ ሳይሆን የኩባንያ መልካም አሰተዳደር ሰራቸው ጠንካራ በመሆኑ ነው ብለዋል :: በመሆኑም ይህንን የኩባንያ መልካም አስተዳደር በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲስፋፋ አዲስ ቻምበር የጀመረውን እንቅስቃሴ የሚያበረታታ መሆኑን ጠቁመዋል :: በተለይ አሁን ላይ ብዙ ኩባንያዎች እና ኢንቨሰተሮች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ መሆኑን ጠቁመው ንግድ ምክር ቤቱ የጀመረውን እንቅስቃሴ አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል::

# አራተኛው ዙር የስራ አስፈጻሚዎች መድረክ በባንኪንግ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ ልምድ ያካበቱትን አቶ በቃሉ ዘለቀን እንግዳ በማድረግ ተካሄደ



**በስታፍ ሪፖርተር**

በአዲስ ቻምበርና በሳክ የስልጠና እና አማካሪ ድርጅት በትብብር የሚሰናዳው የስራ አስፈጻሚዎች መድረክ በተሳካ ሁኔታ በአዲስ አበባ ኢንተር ላግዠሪ ሆቴል ተካሂዷል:: ሁለቱ ተቋማት የሚያዘጋጁት ይህ ወሳኝ መድረክ ለአራተኛ ጊዜ የተካሄደ ሲሆን በዚህኛው ዙር ደግሞ በባንኪንግ ኢንዱስትሪ ውስጥ ከፍተኛ ልምድና ተሞክሮ ያካበቱት ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ለበርካታ አመታት በፕረዚደንትነት ያገለገሉትን አቶ በቃሉ ዘለቀን በእንግድነት አቅርቧል::

አቶ በቃሉ ዘለቀ ከ25 አመታት በላይ ከጀማሪ የባንክ ባለሙያ እስከ ፕረዚደንት ድረስ በማገልገል ለባንኪንግ ኢንዱስትሪው ማደግ የበኩላቸውን አስተዋጾ አድርገዋል:: አቶ በቃሉ በአሁኑ ወቅት የአቢሲኒያ ባንክን በፕዚደንትነት እያገለገሉ ሲሆን በርከት ባሉ ተቋማት የቦርድ አባል በመሆን ሰርተዋል:: ከነዚህም መካከል የኢትዮጵያ ምርት ገበያ፤ኢትዮ ቴሌኮም፤ የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ተጠቃሽ ናቸው::

Leadership in Influence በሚል መሪ ቃል የተካሄደው የስራ አስፈጻሚዎች መድረክ ላይ የካበተ ልምዳቸውን ያካፈሉት አቶ በቃሉ አንድ መሪ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ግልጽ የሆነ ራእይና ግብ ሲኖረው እንዲሁም ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ስትራቴጂ መንደፍ እንዲሁም ብቃት ያለው የሰው ኀይል መመደብ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል::

ከዚህም ባለፈ አንድ መሪ ተቋምን ዘላቂ ለማድረግ ከፈለገ ከባለ ድርሻ አካላትና አጋሮች ጋር ያለውን ግንኙነት ላይ መስራት እንደሚገባ፤ ወደፊት ለሚያጋጥሙ መልካም እድሎችን እና ተግዳሮቶችን ከወዲሁ ማሰብ፤ ከስህተቶች መማር፤ ጽኑ መሆን፤ እራስን የመምራት ክህሎት ማዳበር፤ በየጊዜው ራስን በእውቀት መገንባት አንድን መሪ ስኬታማ እንደሚያደርገው የረጅም ጊዜ ልምዳቸውን አካፍለዋል::

በዶ/ር አደራ አብደላ አወያይነት የተካሄደው አራተኛው ዙር የስራ አስፈጻሚዎች መድረክ በርካቶች የተሳተፉበት ሲሆን እንዲህ አይነት መድረኮች ሀገር በቀል የአመራር እውቀቶች ተተኪ ወጣት መሪዎች ልምድና እውቀትን የሚቀስሙበት እንዲሁም ዘላቂ የሆኑ ተቋማትን ለመገንባት የሚያስችል ጠቃሚ መድረክ ነው ያሉት ደግሞ አቶ ዘካርያስ አሰፋ የንግድ ምክር ቤቱ ምክትል ዋና ጸሀፊ ናቸው::

በዚህ የስራ አስፈጻሚዎች መድረክ ላይ በመገኘት የመዝጊያ ንግግር ያደረጉት የምክር ቤቱ ፕረዚደንት መሰንበት ሸንቁጤ አቶ በቃሉ ዘለቀ በኢትዮጵያ የባንኪንግ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ያበረከቱት አስተዋጾ ከፍተኛ እንደሆነ ተናግረዋል:: አክለው እንዳሉት አቶ በቃሉ የባንክ ባለሙያዎች አቅም እንዲገነባ የነበራቸው ሚና ጉልህ እንደሆነ ተናግረዋል::

ከዚህም ባለፈ በአዲስ ቻምበር አነሳሽነት የተጀመሩት የልምድ ልውውጥ መድረኮች በአሁኑ ወቅት የሚስተዋሉ የአመራር ክፍተቶችን ለመሙላት እና ችግሮችን ለመቅረፍ ወሳኝ ሚና አላቸው ብለዋል ፕረዚደንቷ::

# የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ 19ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን አካሄደ



**በስታፍ ሪፖርተር**

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት( አዲስ ቻምበር) ፕሬዝዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል የሆኑበት የኢትዮጵያ ስፔስ ሳይንስ ሶሳይቲ 19ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ያካሄደ ሲሆን በጉባኤው ላለፉት ሃያ አመታት በበላይ ጠባቂነት ሲያገለግሉ የነበሩትን አቶ ተፈራ ዋልዋ በአቶ ደመቀ መኮንን ተክቷል።

# የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናና ትምህርት ፖሊሲ ጊዜው የሚጠይቀውን ባለሙያዎች እንዲያፈራ አዲስ ቻምበር ጥረት እያደረገ ነው

**በይድነቃቸው ዓለማየሁ**





ለንግድ ም/ቤቱ ሠራተኞች በተዘጋጀው ሥልጠና ላይ እንደተገለጸው በቴክኒክና ሙያ ስልጠናና ትምህርት ፖሊሲ ላይ ከሚነሱ ሕጸጾች መካከል የኩባንያዎች የባለሙያ ፍላጎት እና የሥልጠና ዘርፎች አለመጣጣም አንዱ መሆኑ ተነግሯል። የአዲስ ቻምበር ምክትል ዋና ጸሐፊ አቶ ስዩም ጫኔ ስልጠናውን ሲያስጀምሩ ባስተላለፉት መልዕክት በርካታ የግል ኩባንያዎች ልዩ የሙያ ክህሎት ለሚጠይቁ የቴክኒክ ችግሮች ሲያጋጥማቸው በውጪ ምንዛሬ ቀጥረው እንደሚያሰሩ ገልጸዋል። ይህንን የአቅርቦት ችግር ለመሙላት በሥልጠና ፖሊሲው ላይ የባለድርሻዎች ምክክር አስፈላጊ ነው ብለዋል። በዚህ መሠረት አዲስ ቻምበር መድረኮችን በማዘጋጀት፣ምርምሮችን በማካሄድ የፖሊሰ ማሻሻያዎች እንዲረጉ ዝግጅት እያደረገ መሆኑ ተነግሯል። ከዴንማርክ እና ከኬንያ በመጡ ባለሙያዎች የአገራቸውን ተጨባጭ ተሞክሮዎችን ያካፈሉ ሲሆን በተለይ በጎረቤት ኬንያ ፖሊሲ ለቴክኒክና ሙያ ለተማሪዎች የሥልጠና ወጪ ድጎማ ማድረግን ጨምሮ በርካታ የማበረታቻ ዕድሎችን ይሰጣል ተብሏል። ሚ/ስ አንያ ትሬየር የዴንኒሽ አንደስትሪ ከፍተኛ አማካሪ በበኩላቸው ከፍተኛ ቁጥር ያለው የወጣቶች አገር የሆነችው ኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ፖሊሲዋን በማጠናከር ዕድገቷን ለማፋጠን ብቻ ሳይሆን ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ ይረዳል ብለዋል።

# አሰተሳሰባችንንና አመለካከታችንን ብቻ በመቀየር ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ተገለፀ።




**በከፍያለው ዋሲሁን**

ይህ የተባለው የአዎንታዊ አስተሳሳብ ለኢትዮጵያ ማህበር የተመሰረተብን አንደኛ አመት በዓሉ ሲከበር ነው ። ማህበሩ ሀሙስ ሰኔ 27 ቀን 2016 ዓ.ም አንደኛ አመት ምክንያት በማድረግ አባላቱን በመጥራት የሰራቸውን ስራዎችን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥቷል ።

የማህበሩን መመሰረት ምክንያት ያብራሩት የማህበሩ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ በቀለ ፀጋየ መልካም እና ቅን አስተሳሰብ በኢትዮጵያ እንዲፈጠር በማለም መሆኑን ገልፀዋል ።በመሆኑም ማህበራቸው ( አዎንታዊ አስተሳሰብ ለኢትዮጵያ ) ሰኔ 16 2015 ምስራታውን ይፋ ካደረገ በኃላ ፤ ባለፈው አንድ አመት የተለያዩ ስራዎችን መሰራቱን አቶ በቀለ ተናግረዋል ።ይህውም ማህበሩን በማደረጃት እና እንዲጠናከር በማድረግ ሰለ አዎንታዊ አስተሳሰብ ምንነትና ጥቅሙ ፤ እንዲዚሁም የአዎንታዊ አሰተሳሰብ ተቃራኒ የሆነው አሉታዊ አስተሳሰብ የሚያስከትለውን ግላዊና ሀገራዊ ጉዳቶች ለመማርና ለመገንዘብ ችለናል ብለዋል።

በተጨማሪም ባለፈው አንድ ዓመት በርካታ የዝግጅትና የማደረጀት ስራ ስሰራ ቆይቷል ያሉት አቶ በቀለ ፤ በዚህም የአዎንታዊ አመለካከት ፅንሰ ሃሳብ ፣ የማህበሩን ራዕይ ተልዕኮና እሴቶች ማዘገጃት መቻሉን ገልፀዋል ። በተጨማሪም መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሆኑት ከትምህርት ሚንስቴርና ሰላም ሚንስቴር ፤ ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ጋር ግንኙነቶችን መፍጠር መቻሉንም ነው የተገለፀው ።

ማህበሩ በሰላም ፣ መልካም አስተዳዳር ፣ ማሻሻልና ፣ በድኅነት ቅነሳ ላይ ምክረ ሃሳቦችን አዘጋጅተን ለሚመለከታቸው አካላት ለማቅረብ ማህበሩ እየተዘጋጀ መሆኑንንም አቶ በቀለ ተናግረዋል። አዎንታዊ አስተሳሰብ ለህዝባዊ እድገት በሚል ርዕስ የፓናል ውይይት የተካሄደ ሲሆን በዚህም አዎንታዊ አስተሳሰብ በትምህርት ፣ በጤና ፣ በንግድና በሚዲያ ላይ ያለውን ጠቀሜታ የተመለከቱ ሃሳቦች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል ። አቶ በቀለ አክለውም አሁን ላይ በሀገሪቱ ሚስተዋሉ ችግሮች ምንጭ የአስተሳሰብ መዛነፍ የመነጨ መሆኑን ጠቅሰው ሁሉም አካላት በቅንጅት ሊሰሩ ይገባል ብለዋል ።በመሆኑም አሰተሳሰባችንንና አመለካከታችንን ብቻ በመቀየር ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ገልፀዋል ። ማህበሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሳተመወን አዎንታ የተሰኝ መጽሄትም ያስመረቀ ሲሆን ከዚህ በኃላ በየሶስት ወሩ አሊያም በየስድስት ወሩ እየታተመ ለአንባቢያን እንደሚያደርስ ለማወቅ ችለናል ።

# ኢትዮጵያ ወደ አጎዋ (AGOA) እንድትመለስ ሊፈቀድላት ይገባል

**በሙሉጌታ ጉደታ**




የአፍሪካ የእድገትና የአዲስ እድል ህግ (አጎዋ) ተብሎ የሚታወቀው አሰራር ከተመረጡ የአፍሪካ አገሮች ወደ አሜሪካ ለሚላኩ ሸቀጦች ከቀረጥ ነፃ የማስገባት እድል የሚፈጥር ህግ ነው። የአጎዋ ጥቅሞች በተለየም ከአፍሪካ ወደ አሜሪካ ገበያ ከቀረጥ ነፃ በሚላኩ ሸቀጦች አማካይነት ለተለያዩ አገሮች ያስገኛቸው ጥቅሞችና እድሎች በአሃዝ የሚሰላና በአይን የሚታይ በመሆኑ የሌሎችን አገሮች ቀልብ መሳብ የቻለ እድል ለመሆኑ ተጨባጭ መረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ያም ሆኖ ግን ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ ከአጎዋ ተሳትፏቸው ለጊዜውም ቢሆን ከተገለሉት ጥቂት የአፍሪካ አገሮች አንዷ ሆናለች።

አጎዋ እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በሜይ 2000 ወደ ተግባር ሲገባ ሙሉ ለሙሉ የንግድ ወይም የኢኮኖሚ አላማዎችን አንግቦ እንደ ነበር የሚታወስ ነው። ትንሽ ቆይቶ ግን አጎዋ የአሜሪካን ዲፕሎማሲ ማራመጃ ጭምር መሳሪያ ሆኖ ሲተገበር ተስተውሏል። ዲፕሎማሲ በአገሮች መካከል ለሚካሄደው በጋራ ጥቅም ላይ ለተመሰረተ ግንኙነትና የኢኮኖሚ ትብብር ሁነኛ መሳሪያ ነው። ይህ ካልሆነ ግን በከፍተኛ የወጣት ስራ አጥነትና የድህነት ችግር ውስጥ የሚገኙ የአፍሪካ አገሮች ከአጎዋ በሚገለሉበት ወቅት ለተጨማሪ ጉዳት ይዳረጋሉ። የግሉ ሴክተር አምራች ድርጅቶች እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል። አጎዋ በተለይ በማደግ ላይ ላሉ የግሉ ሴክተር ተቋሞች ትልቅ የእድገት ተስፋ ሆኖ እያገለገለ ነው። ስለሆነም ተጨማሪ የአፍሪካ አገሮች ወደ አጎዋ መግባት አለባቸው እንጂ ያሉት መቀነስ የለባቸውም።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያ የመንግስት ሴክተሩ በኢኮኖሚው ውስጥ በነበረው የበላይነት የግሉ ሴክተር በሚገባው መጠን እንዳያድግ ማነቆ ሆኖበት ቆይቷል። ይህም በበኩሉ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቬስትመንትን ፍሰት ሲያውክ ተስተውሏል። አገሪቷ ከአጎዋ መገለሏ ደግሞ ሁኔታውን አባብሶታል። በመተግበር ላይ የሚገኘው የኢኮኖሚ ማሻሻያ የፖሊሲ ብዙ ነገሮችን የለወጠ ቢሆንም ቅሉ በአለም አቀፍ ድጋፍና ትብብር ካልታጀበ የተጠበቀውን ውጤት ማግኘት ያዳግታል። ከአጎዋ መገለል ደግሞ የተፈጠረውን ተስፋ አደብዝዞታል። የግሉ ሴክተር ይበልጥ እንዲዳከም አድርጎታል።

በኢትዮጵያና በአሜሪካ መካከል የሚካሄደው የኢኮኖሚ ትብብር ሂደት የፖለቲካ ተፅእኖ በሚያርፍበት ወቅት በተጠበቀው መጠን ተጠናክሮ ሊቀጥል አይችልም። ለረጅም ጊዜ የአገራችን የግሉ ሴክተር ኩባንያዎች ወደ አሜሪካ የሚልኳቸው ምርቶች በመጠን እየቀነሱ የመጡበት ዋናው ምክንያት፣ በሁለቱ አገሮች መካከል የሚካሄደው ግንኙነት በፖለቲካ ውጣ ውረድ የተቃኘ በመሆኑ ነው። አሜሪካ በአለማችን ትልቁን ኢኮኖሚ የገነባች እንደመሆኗ መጠን የኢትዮጵያን የግል ሴክተር ለማጠናከርና ወደ እድገት ጎዳና እንዲገባ ለማገዝ ትልቅ አቅም አላት። ይህ ግን ከቃላት ያላለፈና እስከ ዛሬም በተግባር ያልተተረጎም አባባል ነው።

በተጨማሪም የተለያዩ የፖሊሲ ችግሮች በሁለቱ አገሮች ኢኮኖሚ መካከል ጠንካራ መተባበር እንዳይኖር አድርገዋል። ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ካሉት አገሮች መካከል የእድገት ተስፋዋ ከፍተኛ የሆነች አገር ናት። ስለሆነም የአሜሪካ የግሉ ኢኮኖሚ ለኢትዮጵያ የግል ሴክተር ማደግ ወይም መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅ ማድረግ ይጠበቅበታል። የአገራችን የግል ሴክተር ኩባንያዎች ወደ አሜሪካ የሚልኳቸው ምርቶች በብዛትም ሆነ በጥራት እያደጉ እንዲሄዱ አጎዋን የመሳሰሉ የንግድ እድሎች መከፈት ይኖርባቸዋል።

ለኢትዮጵያ ከአጎዋ መገለል ማለት የግሉ ሴክተር እየቀጨጨ እንዲሄድ ማድረግ ማለት ነው። ይህ ደግሞ የአሜሪካ ከአፍሪካ ጋር ያላትን የትብብር ፖሊሲና መንፈስ የሚረብሽ አካሄድ ይሆናል። አሜሪካ የአፍሪካ አገሮች እንደኛዋ ታላቅ የልማት አጋር መሆኗ የአደባባይ ምስጢር ነው። በአፍሪካ ቀንድ ያላትም ተፅእና ከፍተኛ ነው። በዚህ የኢኮኖሚ ውድድር በበረታበት አለም አሜሪካ አፍሪካ እንዲጠናከር እንጂ እንዲዳከም እንደማትፈልግ የታወቀ ነው። ስለዚህም ኢትዮጵያን ከአጎዋ ጥቅሞች ማግለል የፖሊሲዋ አላማ ስላልሆነ አገራችን በቅርብ ጊዜ አጎዋን እንድትቀላቀል ውሳኔ ማድረግ ይጠበቅባታል።

አገራችን ከአጎዋ በመገለሏ በግሉ ሴክተር ላይ የደረሰው ጉዳት በተጨባጭ ጥናት የተደገፈ ባይሆንም በአጠቃላይ ግን አያሌ የስራ እድሎች ተዘግተዋል። አያሌ አምራች ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን በመጠን እንዲቀንሱና ሌላ ገበያ እንዲፈልጉ ተደርገዋል። በዚህም ምክንያት ለተጨማሪ ወጪዎች ተዳርገዋል። የምርት ሂደታቸው ተስተጓጉሏል። የምርት መጠናቸው ቀንሷል። በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣት ስራ አጦች ስራ እንዳያገኙ ሆነዋል። አገሪቷ ልታገኝ የምትችለውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እንድታጣ ተገድዳለች። ይህም በአጠቃላይ በኢኮኖሚው ላይ አያሌ አሉታዊ ተፅእኖዎች እንዲያርፉበት ሆኗል።

በእነዚህ ሁኔታዎች የተነሳ ነው እንግዲህ ኢትዮጵያ ወደ አጎዋ መመለሷ ለኢኮኖሚው ወሳኝ ጥያቄ የሚሆነው። በተለይም በጥቃቅንና በመካከለኛ አምራቾች አካባቢ በአጎዋ ዘመን ይታይ የነበረው ከፍተኛ መነሳሳትና እድገት አሁን ጨርሶ ስለጠፋና ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ድርጅቶች ስለተዘጉና ከገበያ ውጪ ስለሆኑ አያሌ ቤተሰቦች ገቢያቸው አሽልቆሏል። የዋጋ ግሽበት የህብረተሰቡን ህይወት ክፉኛ ባመሳቀለበት በአሁኑ ጊዜ፣ ከስራ መፈናቀልና የእለት ጉርስ ማጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማንኛውም ወገን የሚረዳው ነው።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አሁንም ቢሆን ከከፍተኛ ድቀት ተላቋል ማለት አይደለም። ላለፉት አርባ አመታት ለሚሆን ጊዜ አገሪቷ በመንግስት የበላይነት በሚመራው የኢኮኖሚ ስትራቴጂ የተነሳ ማደግ ባለባት መጠን ማደግ አልቻለችም። ይህም ሁኔታ በበኩሉ የአገራችንን የግል ሴክተሩ እየቀጨጨ እንዲሄድ አድርጎታል። በአለም ገበያ ተወዳዳሪነቱ እየቀነሰ እንዲሄድ ተገዷል። የእድገት ሞተር ከመሆኑ ይልቅ የግሉ ሴክተር በአሁኑ ጊዜ ለህልውናው የሚታገል ክፍለ ኢኮኖሚ ሆኗል ቢባል ነገሩን ማጋነን አይሆንም።

ከዚህም በተጨማሪም ባለፉት 30 አመታት የተፈጠሩት የግል ባንኮች በሚገባቸው መጠን ባለማደጋቸውና የገንዘብ ተቋሙ በአጠቃላይ ባለመጠናከሩ የተነሳ የውጭ ምንዛሪ እጥረት የኢንቬስትመንት እድሎች እየጠበቡ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል። በዚህ ላይ አገራችን ከአጎዋ ለጊዜውም ቢሆን በመታገዷ ተጨማሪ እሴት እንዳይፈጠርና የኢኮኖሚ መረጋጋት እንዳይመጣ እንከን ፈጥሯል። ስለዚህም አገራችንን ወደ ቀድሞው የአጎዋ የንግድ እድል መመለስ ማለት አገራዊ ኢኮኖሚው ወደ ተሻለ የማገገምና የእድገት ሂደት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል ማለት ነው።

ለረጅም ጊዜ የአሜሪካ የኢኮኖሚ ድጋፍ ያተኮረው በመንግስታቱ መካከል በሚደረጉ የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ብቻ ነበር። የአገራችን የግል ሴክተር ከእንደዚህ አይነቱ ግንኙነት በመጠኑም ቢሆን ተጠቃሚ የነበረ ቢሆንም ውጤቱ ግን ሁኔታዎችን በወሳኝነት የሚለውጥ አልነበረም። በኢንቬስትመንት፣ በውጭ ምንዛሪ ወይም በመዋእለ ንዋይ ፍሰት፣ በቴክኖሎጂ፣ በእውቀት ሽግግር፣ በቢዝነስ አስተዳደር ረገድ ሊገኙ የነበሩት ጥቅሞች ሊተላለፉ አልቻሉም። አጎዋ ግን እነዚህን ጥቅሞች ለአገራችን ኢኮኖሚ ለማስገኘት አንዱ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። አጎዋ ግን በሁለቱ አገሮች መካከል ለሚመሰረተው አዲስ የትብብር ግንኙነት የመሰረት ድንጋይ ሊያስቀምጥ ይችላል። አሜሪካ ለግሉ ሴክተር እድገት የምታደርገውን እርዳታ አጠናክራ እንድትቀጥልበትም ሊያደርጋት ይችላል። ባለፈው ተሞክሮ መሰረት አጎዋ በረጅም ጊዜ የሚሰጠው የንግድ ጥቅሞች ሁለገብና ጥልቀት እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል።

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

Addis Chamber Training Institute

## An Invitation to Attend a Training Course Entitled:

# Business Plan Preparation

### Training Date, Time and Venue:

From July 29 – August 2, 2024 for five half days from 1:30PM - 5:30PM in the afternoon at **Wabi Shebele Hotel.**

### Objective of the Training:

- To enhance trainee's skill and capacity to develop effective and standardized business plan

### Course Contents:

- What is a business plan?
- What does a business plan do?
- Do I need a business plan? What can happen without a plan?
- Why take time to build a business plan?
- What key elements a business plan should include?
- How do you develop a new business from an idea?
- How do you develop the complete business plan?
- How do you evaluate/ test business plan effectiveness?
- What is a financer looking for in business plan?

### Target groups:

Business Owners, Managers, Department Heads, Experts and others interested to attend this important training.

### Training fee:

Birr 4,250 per person for members and Birr 5,100 per person for non-members.

### For registration and inquiries:

0115 500934 / 0115 518 055 Ext. 215, 0913249766, 0911194965, 0911343078, 0913553393
addischambertraining3@gmail.com; assefakasa2@gmail.com & hiwottlhn9@gmail.com




አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# የኢትዮጵያ ወደ አጎዋ (AGOA) እንድትመለስ ሊፈቀድላት ይገባል...

ከ ገጽ 5 የዞረ

እንዳለመታደል ሆኖ የአገራችን የግል የንግድ ተቋሞች ከእንደዚህ አይነቱ መልካም አጋጣሚ ተጠቃሚ ሊሆኑ አልቻሉም:: ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከትልልቆቹ የቡና ላኪ አገሮች ተርታ የምትሰለፍ ብትሆንም፣ ወደ አሜሪካ ገበያ የምትልከው የቡና መጠን ከፍተኛ እድገት አላስመዘገበም:: የጨርቃጨርቅና የቆዳ ኢንዱስትሪዎች ምርቶቻቸውን ወደ አሜሪካ በመላክ ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ ማስገኘት ሲችሉ ይህንን ማድረግ ሳይችሉ ቆይተዋል:: ኢትዮጵያ የአጎዋ የንግድ ጥቅሞች ተጠቃሚ ስትሆን ግን እነዚህን እስከዛሬ ያልተገኙትን ጥቅሞች ማግኘት ትችላለች::

ከአጎዋ የንግድ እድሎች ተጠቃሚ የሚሆኑ የአፍሪካ አገሮች ቁጥር አነስተኛ ነው:: ጥቂቶቹ አገሮች ከፍተኛ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ እነዚህን ጥቅሞች በሚገባ ሊያገኙ አልቻሉም:: ለምሳሌም ኡጋንዳ ከአጎዋ እድል የተሻለች ተጠቃሚ መሆኗ ይነገራል:: በአንፃሩ ደግሞ የአገራችን የግሉ ሴክተር ተዋናዮች ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅሞች ሳያገኙ ቆይተዋል:: አሁን ደግሞ ጭራሹን ከአጎዋ ተገልለዋል:: ለዚህም ሁኔታ መከሰት ከብዙ ምክንያቶች ጥቂቶቹን ለመጥቀስ መዋቅራዊ ድክመቶች እንዲሁም የኢንቬስትመንት አቅርቦት እንደልብ አለመገኘት መሆኑ ይነገራል:: ይህም ማለት ግን ሁሉም የአገራችን የንግድና የኢንዱስትሪ ተቋሞች ከአሜሪካ ገበያ መልካም አጋጣሚዎች ምንም አልተጠቀሙም ማለት አይደለም::

የአሜሪካ አስተዳደር ለአገራችን የግል ሴክተር እድገት መልካም አመለካከት እንዳለው ይታወቃል:: የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ እድገት ለአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ጭምር መልካም የመረጋጋት እድል ይዞ እንደሚመጣ የታወቀ ነገር ነው:: ነገሩ ከዚህ አንፃር ሲታይ አገራችን አሁኑኑ ከአጎዋ የንግድ ጥቅሞች አትራፊ እንድትሆን ማድረግ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው:: ይህ ሲሆን ነው በአሜሪካና በአገራችን መካከል ከረጅም ጊዜ ጀምሮ የተገነባው ግንኙነት ወደፊት እየዳበረ የሚሄደው ወይም ወደ ቀድሞ ተስፋ ሰጪ ሁኔታው ሊመለስ የሚችለው:: ይህ እንዲሆን ግን አሜሪካ ለኢትዮጵያ ወደ አጎዋ የመመለስ ጥያቄ ያልተቆጠበ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅባታል:: በእርግጥም ኢትዮጵያ ወደ አጎዋ እንድትመለስ ሊፈቀድላት ይገባል!



አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

# Business Consultancy Service from Addis Chamber

*Let Us Make it Come True*



- Business Plan Preparation
- Strategic Plan Preparation
- Feasibility studies,
- Business Clinic, etc...

contact us:
Mexico Square, Chamber Building
+251-115155221, +251-11518055 ext 218
+251931558929
marketing@addischamber.com,
flijalem4@gmail.com
www.addischamber.com

# ADDIS CHAMBER

አዲስ ቻምበር
ADDIS CHAMBER

Institute of Directors Ethiopia

***Development of effective board leadership and application of best practices in corporate governance***



## SERVICES FOR DIRECTORS

- Certification Program
- Training Program
- Board Evaluation
- Standards and Codes
- Consultancy and Advisory Service
- Access to Certified Directors' database
- Recommending candidate directors
- Peer networking and forums
- Research and advocacy
- Publication

Mexico Square, Chamber Building
. +251 115155221
Iod.aaccsa@gmail.com
www.Addis chamber .com

Addis Chamber Training Institute

## An Invitation to Attend a Training Course Entitled:

# International Trade Service & Ethiopian Export/Import Practice

### Training Date, Time and Venue:

From July 29- August 2, 2024 for five half days from 8:30 a.m. - 12:30 p.m. in the morning at Wabi Shebele Hotel.

### Objective of the Training:

- To enable participants acquire a thorough understanding of International Trade and Documentary Requirements and develop the skill in clear identification and determination of their contents and to understand import and export procedures of Ethiopia.

### Course Contents:

- International Trade
- Trade Facilitation
- International Banking Operations
- INCOTERMS
- Government Rules in International Trade
- Import/Export Practice in Ethiopia
- The Role of Guarantee in International Trade

### Target groups:

Importers, Exporters, Transitors, Custom Agents and any individual interested to attend this important training.

### Training fee:

Birr 4,250 per person for members and Birr 5,100 per person for non-members.

### For registration and inquiries:

0115 500934 / 0115 518 055 Ext. 215, 0913249766, 0911194965, 0911343078, 0913553393
assefakasa2@gmail.com, hiwottlhn9@gmail.com & dejedesalegn@gmail.com.